ጤና ይስጥልኝ፤

እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሰን።

በዚህ የ2013 የመጀመሪያ ስርጭት ሦስት አጫጭር መታጥፎች አቅርቤአለሁ።

ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ በዚህ ማስታወቂያ በበረከተበትና መታወቂያ በሚያጭበረብርበት ዘመን በመታወቂያና በማስታወቂያ እንዳንወናበድ የሚያሳስብ ነው።

ፈላሻ? ሁለት ዋና ዋና አሳቦች የተሰናሰሉበት መጣጥፍ ነው። የመጀመሪያው እርግማንን የሚመለከት ሆኖ ክርስቲያኖች እውን የእርግማን ስለባዎች ናቸው? ክርስቲያኖች ፈላሻዎችን ስለረገሙ አብርሃምን የመርገም ቅጣት ተቀባዮች ናቸው? ንስሐ መግባት ያለባቸው ባለ ዕዳዎች ናቸው? የሚል ሲሆን ሁለተኛውና ሰፋ ያለው ለመሆኑ ፈላሻዎች ማን ናቸው? እስራኤላውያን ናቸውን? በአገራችን የተገኙት ሰዎቹ ናቸው ወይስ ሃይማኖቱ? የሚል ነው።

የመጨረሻው የፊልጵስዩስን መልእክት በመቀጠል የቆምንበትን ሁለት ጥቅሶች የምናጠናበት ነው።

መልካም ንባብ።

ዘላለም መንግሥቱ / ዕዝራ ስነ ጽሑፍ፥







## ደስ፥ ደስ፥ ደስ፥ ደስ

ነገር ግን በእምነታችሁ መሥዋዕትና አገልግሎት ተጨምሬ
ሕይወቴ እንኳ ቢፈስ፥ ደስ ብሎኛል፤
ከሁላችሁም ጋር አብሬ ደስ ብሎኛል፤
እናንተም ደግሞ እንዲሁ ደስ ይበላችሁ፤
ከእኔም ጋር አብራችሁ ደስ ይበላችሁ።

ፊል. ፪፥ ፲፯-፲፰




ከጥቂት ዓመታት በፊት በቅርባችን ከተማ የምትገኝ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ባዘጋጀችው ኮንፍረንስ ላይ እንድንገኝ በተላከልን የማስታወቂያ ወረቀት ላይ የአንድ ቃል አንድ ፊደል ሳይጻፍ ቀርቶ ነበር። የአምልኮ ቦታው ተጽፎ፥ “በ. . . ተገኝተው እንዲያመልኩ እንጋብዛለን” የሚለው ላይ ‘ገ’ ሳትጻፍ ቀርታ፥ “በ. . . ተኝተው እንዲያመልኩ እንጋብዛለን” ይል ነበር። በዚያን ጊዜ በመንፈስ መገኘትስ የሚባለው እጅ ሲጫን ወድቆ ተጋድሞ መቆየት የጊዜው ‘ፋሽን’ ስለነበር እውነትም ተኝቶ ማምለክ ሳይኖር አይቀርም አልን። በማስታወቂያው ጥቂት ሳቅን።

ሌላ ማስታወቂያ ደግሞ በአንድ የመነቃቂያ ስብሰባ ላይ የሚያገለግሉ ሁለት አገልጋዮችን ስም ጽፎ ከስማቸው በፊት የተለመደውና የተወደደው የእንግሊዝኛ ሹመት ቃል (ፓስተር) ተጽፎአል። ግን በስሕተት ፓስተር ሳይሆን ፖስተር ተብሎ ነው የተጻፈው። ለዝግጅቱ ተጎትጉቶ የሄደ አንድ ወንድም በኮንፈረንሱ ይሆናል የተባለውና በማስታወቂያ የተጻፈው ፈውስና ተአምራት ቀርቶ በወጉም የተሰበከ ስብከት ስላጣ አዝኖ በቀኑ መጨረሻ ለጋበዙት ወገኖች፥ “እውነትም እነዚህ ልክ እንደተጻፈላቸው የታወቁ ፖስተሮች ናቸው” አላቸው።

ስለ ማስታወቂያ የሚቀለዱ ብዙ ቀልዶችና ተረቦች አሉ። አንዱ፥ *Samson had the right idea about advertising. He took two columns and brought down the house.* የሚል የቃላት ጨዋታ ወይም ቅኔ ያለበት ነው። ሁለቱን አዕማድ ከሁለት የጽሑፍ አምዶች ጋር አመሳስለው ከጠቅላላው መፍረስ ጋር ማቆራኘታቸው ነው። አንዴ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አንድ ተማሪ ማስታወቂያ ጻፈና ለጠፈ። የጻፈው፥ “ትናንትና አንድ በጣም የሚያምር በውድ ዋጋ የተገዛ ኮፊያዬ ጠፍቶብኛል፤ የት እንደጠፋ አላውቅም፤ ምናልባት ካፊቴሪያ ውስጥ ይሆናል ወይም ላይብረሪ ውስጥ ወይም መማሪያ ክፍል። ብቻ ላገኘልኝ ሰው ወሮታውን እከፍላለሁ” ብሎ የዶርም (የማደሪያ ክፍል) ቁጥሩን ጽፎ ለጠፈ። ከማስታወቂያው ስር ሌላ ተማሪ፥ “ኮፊያውን ብታገኝ በምን ጭንቅላትህ ላይ ታደርገዋለህ? ይልቅስ ኮፊያህን ትተህ ጭንቅላት ብትፈልግ ይሻልሃል” ብሎ ጻፈበት።

ይህን ልጽፍ ያበቃኝን በአንድ ድረ ገጽ ላይ ወደ ኢየሩሳሌም የሚደረግ ጉዞ የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ ደግሞ በቅርቡ አነበብኩ። ቀልቤን የሳበው ቃል፥ “ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ያሉ ታሪካዊ ቦታዎች የሚረገጡበትና የሚባረኩበትን ታላቅ ጉዞ!” የሚለው ነው።

ብዙ የኢየሩሳሌም ጉዞ ማስታወቂያዎች ብሰማና ባነብም ይህኛው በጣም የተለየ ነው። ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ማለት ምን ይሆን? ከነአዳም አገር ከዔድን ጀምሮ የሎጥን አገር አራራትን፥ የአብርሃምን አገር ዑርን፥




የነዮሴፍን አገር ግብጽን፥ የነዮናስን ነነዌ፥ የነአስቴርን አገር ሱሳና ባቢሎንን፥ የነጳውሎስን ሮሜ፥ የነዮሐንስን ፍጥሞ አስጎብኝቶ ከዔድን ገነት እንደጀመረው በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይጠናቀቅ ይሆን ብዬ ገመትኩ! ማስታወቂያው ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ያሉ ታሪካዊ ቦታዎች ነዋ የሚለው! መቼም በቅርብ ባላውቃቸውም አስተዋዋቂዎቹና አስጎብኚዎቹ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች እንደሆኑ ከስዕሉ ይታያል። ሁለት ፓስተሮችና አንድ ዘማሪ አሉበት። ሌሎችም እንደሚኖሩ ያመለክታል። ከሁለቱ ፓስተሮች አንዱ የጉዞው አዘጋጅና ባለራእይ ነው።

እንዲያው ይህ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ የተባለውን የጉዞ ሰሌዳ ለማወቅ ስል በማስታወቂያው ላይ ያለውን ቁጥር ከመደወሌ በፊት፥ “የበለጠ ለመረዳት ከዚህ ይጫኑ” የሚለውን ተጫንኩ። በ16 ገጾች በስዕል ያሸበረቀው የጉዞ ዝርዝር የሚናገረው ሌላ ነው። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተቀበረችበትንና በክብር የተነሣችበትን ፍልሰታ ለማርያም ይነበኛሉ፥ የተገዘዙበትን ቅዱስ ስፍራ ይሳለማሉ፥ ግብረ ሕማማቱን በመስማት ስግደት ሲሰግዱ ይውላሉ [ይህ የፋሲካ ሰሞን ስለሆነ ነው] ይልና ከዚያ ጥብጠባው፥ ዑደቱ፥ እመቤታችን ማርያም ወተት ያጠባችበት የወተቱ ዋሻን መጎብኘቱ፥ ቅዱስ መስቀሉን አጅቦ መጓዙ፥ ጧፍ ይዞ መዞሩ፥ ቅዱሳት መካናትን መሳለሙ፥ በነቢዩ ኤልሳ ስም ከሚጠራው ምንጭ ጸበል መጠመቁ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት ቦታ ዮርዳኖስ መጠመቁ እየተዘረዘረ የ13ቱ ቀናት ጉዞ ይጠናቀቃል። ከጉዞው ራቅ ያለው ቦታ ቀርሜሎስ ሆኖ በኢየሩሳሌምና በዙሪያዋ ያሉትን ቦታዎች እንጂ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ የሚገኙትን ታሪካዊ ቦታዎችን በአሳብም እንኳ አያስዳስስም። እንዲያውም መጠብጠብና ጠበል መጠመቅን፥ መሳለምና መስገድን የመሰሉ የልማዳዊ ሃይማኖት ወጎችና ተግባራትን ይዞአል። በአዲስ ኪዳን የማይገኙ (እንደ ፍልሰታ ለማርያም) የአፈታሪክና የትውፊት ጉዳዮችም አሉበት።

የተምታታ ሆነብኝ። ቁርበቱና ሆድ ዕቃው (ማስታወቂያውና ዝርዝሩ) ተለያዩ። ምናልባት ዝርዝሩ የጉዞ ወኪሉ ዝርዝር ይሆናል አልኩ፤ ግን የአንዱ ማስታወቂያ በር ሲንኳኳ (እዚህ ይጫኑ የሚለውን ሲጫኑት) የሚነበብ ነገር ነው አብሮ የተጻፈውና የጉዞ አስተዋዋቂዎቹ ሳያዩት ወይም ሳያነብቡት ቀርተው አይመስለኝም። ሳያውቁ ቀርተው ከሆነ ስሕተት ነው። አውቀው ከሆነም የበለጠ ስሕተት ነው። ምናልባት፥ “ግድ የለም፥ እዚያ ከደረስን በኋላ የሚጠመቁትና ጧፍ የሚያበሩት በዚያ፥ እኛ ደግሞ በዚህ እንሄዳለን” ብለውም ከሆነ ቢያንስ በማስታወቂያቸው ግልጽ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህ በክርስቲያናዊ ድረ ገጽ ላይ የተለጠፈ ማስታወቂያ በመሆኑ የሚያስተዛዝብና የሚያስገምት ነው። አስለጣፊዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ለጣፊዎቹም ሳያዩት ቀሩ ማለት አይቻልምና

ለጣፊዎቹ የድረ ገጹ ባለቤቶችም መስፈርት አላቸው ወይስ የላቸውም? ለገንዘብ ነው የሚሠሩት ወይስ ለክርስቲያናዊ እሴቶች የሚለውም መጤን ያለበት ጥያቄ ነው። ማስታወቂያ ያወናብዳል።

እንዲህ ያለ ማስታወቂያና መታወቂያ የሚሠሩ "አገልጋዮች" ግባቸው ምንድርነው? ይህን መሳይ እርምጃ የእነዚህን ሰዎች ንግግራቸውን፥ ስብከቶችና ትምህርቶቻቸውን ብቻ ሳይሆን አስተምህሮዎቻቸውንም እንዲጠየቅ ያደርገዋል። አሳች ማስታወቂያ በብዙ አገሮች የሚያስቀጣ ወንጀል ነው። በምዕራቡ ዲሞክራሲያዊ ዓለም ከተራ ማስታወቂያ እስከ ንግድ ምልክት የተቀመጡ ደንቦች ሲኖሩ እነዚህን ደንቦች የሚተላለፉ ነገሮች ከተፈጸሙ ከማስተካከያ እስከ ቅጣት የሚደርሱና ከዚያም ተከትሎ የሚደረጉ የማስተካከያ እርምጃዎች በግልጽ ተጽፈው ተቀምጠዋል።

ማስታወቂያ ያወናብዳል። ዱሮ በደርግ ዘመን መጀመሪያ በአንድ የፍተሻ ኬላ ላይ የራሱ ያልሆነ መታወቂያ የያዘ ወጣት ተገኝና ፈታሹ እየሳቀበት፥ "ማሞ ሌላ ሜታዎቃው ሌላ፤ ቲሄዳሌሽ ዎዴ ዎፌ ላላ" ብሎ ከመኪናው አወረደው። መታወቂያና ሰውነት የተለያየ ሲሆን ችግር አለ። ጥንት ቴአትር የሚሠሩ ባለሙያዎች ወደ መድረክ ይወጡና አንድ ሰው ሆነው ይሠሩና ተመልሰው ወደ መልበሻ ክፍል ገብተው ሌላ ለብሰው ሌላ ሰው ሆነው ይመጣሉ። ብዙ ጊዜ ሴቶች ተዋናዮች የሉምና እንደ ሴት ሆነው የሚሠሩትም ወንዶች ናቸው። እንደ ሴት ብቻ ሳይሆን እንደ ሽማግሌም እንደ ወጣትም እንደ ሌላውም ሁሉ እየሆኑ ነው የሚሠሩት። እና አንዳንዴ የሚለብሱትና እየሆኑ ያሉት የሚወክሉት ሰው ማንነት ይምታታባቸዋል። እንደ ሴት ተኳኩለው ይወጡና እንደ ወንድ ሆነው ይሠራሉ፤ ወይም እንደ ሽማግሌ ለብሰው ድምጻቸውን አቅጥነው የሴቷን ሚና ይጫወታሉ። ያኔ ተመልካቾቹ መሳቅ ብቻ አይደለም፤ ቲማቲምና እንቁላል ይዘው እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋልና ያንን ወርውረው እየመቱአቸው "ሁፖክሪስ!" ብለው በመጮኽ ያፌዙባቸዋል። እየሆኑ ያሉትና እየወከሉ ያሉት የተለያዩ ናቸው። ሁፖክሪስ በግሪክ ልሳን ግብዝ ማለት ነው። ጌታ ጻፎችና ፈሪሳውያንን ስለግብዝነታቸው አጠንክሮ ነቅፎአቸው ነበር። ግብዞች ራሳቸውን የሚያታልሉ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችንም የሚያስቱ ናቸው። በብዙዎች ዘንድ በገሃድ አይታዩ ይሆናል፤ ግን በጥቂቶችም ከታዩ መታየት ነው። ጳውሎስ በ1ተሰ. 2፥10 ላይ ስለኑሮው ሰዎችንም እግዚአብሔርንም ምስክር ይጠራል።

ይህ አሳብ ስለ ማስታወቂያዎችና መተዋወቂያዎች እንዳስብም አደረገኝ። ከላይ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ያሉ ታሪካዊ ቦታዎችን በሚያስነበኘው ማስታወቂያ ባነበብኩበት እና በሌሎችም ድረ ገጾች የሚገርሙና እጅግ የተጋነኑ ማስታወቂያዎች ይነገራሉ። በተለይ የፈውስና የተአምራትን ማስታወቂያዎች ስናጤን ከመስመር የወጡ፥ ብቻ ሳይሆኑ የሚያስተዛዝቡና የሚያስጠይቁም ናቸው። ከዚህ በፊት ብዙ የተነገረላቸው ኮንፍራንሶችን ተገኝቼ የተነገሩትን ነገሮች ግን አጥቼባቸዋለሁ። አገልጋዮቹ ከላይ የተጠቀሰው ወንድም፥ "እውነትም ፖስተሮች ናቸው" እንዳለው መለከቱ ይጎላና ሰዎቹ ያንሳሉ። ትሕትና በአፍጢሙ ይደፋል። የሰዎች ፍላጎት ያይልና የሚዘገነው ጉም ይሆናል። ማስታወቂያው ይነሰነስና የሚለቀመው የሰንበት መና ይሆናል።

ተአምራት ይደረጋሉ ተብሎ ሳይሆኑ፥ ሳይደረጉ ከሚቀሩ ምን አለበት ሳይነገር ቢቀርና ተአምራቱ ግን ቢኖሩ? ነገሮቹ ከተፈጸሙ ምንም ችግር አይሆንምና ተአምራቱ ከኖሩ መነገሩ ክፋት የለበትም። ካልኖረ ግን አሳፋሪ ይሆናል። ሳይፈጸሙ ሲቀሩ አስተዋዋቂዎቹና ተዋዋቂዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ወደዚህ የራሳቸው የስንፍና ውርርድ ውስጥ ያስገቡት የእግዚአብሔር ስምም ይሰደባል። 'እምነት' የሚሉት የጆከር ካርታቸው የድብስብስ ጨዋታ የመጡትን የተአምራትና ፈውስ አፈንፋኞች ስሜትና ቀልብ ወደ ላይ ያጉነዋል። በእውነት የአካል ፈውስ የሚሹቱ ግን ከቃሬዛና ዊልቸር፥ ከምርኩዝና ከዘራ ጋር ሲመለሱ በጉዳታቸው ላይ ሞራላዊና መንፈሳዊ የእምነት ተቃውሶ ተመርቆላቸው ነው። ለዚህ ነው፥ ምን አለበት ማስታወቂያው ሳይነገር ቢቀርና ተአምራቱ ግን ቢኖሩ? ያልኩት። የተተነበዩት ተአምራት ቢኖሩ ምንም ክፋት የለበትም። ካልኖሩ ግን ያስጠይቃል።

ከዓመታት በፊት አገለግልበት በነበረች በደብረ ዘይት ከተማ አንድ ስመ ገናና አገልጋይ ተጋብዞ የመጣ ጊዜ የተደረገው ይህ ነበር። ዝናው ከአገልግሎቱ ቀናት ቀድሞ ተነዛ፤ የፈውስ ማስታወቂያ ተለፈፈ፤ በቀኑ ብዙ ሕመማን መጡ። ከወዲያ ዝናው ስለቀደመ፥ ከወዲህ ደግሞ ጉጉቱ ብዙዎችን ጠራ። በቀኑ ብዙ በዊልቸር የተቀመጡ፥ በደጋፊ ተይዘው የመጡም የሚታዩ ድውያን ነበሩ። ፈውሰኛው ግን የኩላሊት ጠጠር፥ የሐሞት ከረጢት ጠጠር፥ የእግር መሸምቀቅ፥ የማኅጸን ሕመም፥ የግራ ጎን ውጋት፥ እየጠራ ብዙዎች እንደተፈወሱ አወጀ። ከሚታዩቱ ከፊት ከተኮለኮሉቱ አንድም የተፈወሰ አልነበረም። ተፈወሱ ከተባሉትም በቅርብ የማውቃቸው ነበሩና አለመፈወሳቸውን ሳይሰነብት አረጋግጫለሁ። ማስታወቂያውን ወደ ጎን ትተነው እንኳ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የታየው ዓይነት ፈውስ ከቶም አይደለም።

ነቢዩ ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ እግዚአብሔር በእሳት እንደሚመልስ ለተሰበሰበው ሕዝብና ለበኣል ነቢያት ተናገረ፤ 1ነገ. 18፥20-24። ይህ ማስታወቂያ ነው ማለት ይቻላል። ውርርድ ነው። በመስዋዕተ ሠርክ ግን እሳቱ ባይወርድ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? እግዚአብሔር ሳይሆን በኣል የተባለው ጣዖት አምላክ መሆኑ ይቀጥል ነበር። ኤልያስ ይገደል ነበር። በእርግጥ ይገደል ነበር። የእግዚአብሔርም ስም ይዋረድ ነበር። *ሰምቶም በእሳት የሚመልስ አምላክ፥ እርሱ አምላክ ይሁን* ብሎ ነበርና ምንም እንኳ በኣል ባይመልስም እግዚአብሔርም አልመለሰም ተብሎ አይመለከም ነበር። ይህ ለውርርድ ቢቀርብም የተፈጸመ 'ማስታወቂያ' ነው። በሌሎች ቅዱሳን አገልግሎት፥ በተለይም በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚያሳስት ማስታወቂያ አይነበብም። እንዲያውም በጭራሽ የፈውስና የተአምራት ማስታወቂያዎች አይነገሩም። ፈውሶችና ተአምራቱ ግን ጥሩምባና መለከትም ሳይነፋ ይደረጉ ነበር። ዛሬም በምሰሶና በግድግዳ ላይ ሳይለጠፍ፥ በሬድዮና በመጽሔትም ሳይታወጅ፥ በድረ ገጾችም ማስታወቂያ ሳይረጭ እግዚአብሔር መሥራት አይቻለውም? ተአምሩ ቀድሞ ጥሩምባው ቢከተል ምንኛ መልካም ነበር! ማስታወቂያ ያወናብዳል።

ባለፈው (ዕዝራ ቁጥር 19) የመግቢያ ገጽ እንዳልኩት (ፕሬዚደንት አባማን መታወቂያ እንደጠየቀችው ሴት) መታወቂያ ይጠየቃል። ሲጠየቅ ግን ማሞና መታወቂያው መመሳሰል ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ዘመን፥ በተለይ በዚህ ማስታወቂያ በበረከተበትና መታወቂያ በሚያጭበረብርበት ዘመን በመታወቂያና በማስታወቂያ እንዳንወናበድ ጌታ በማስተዋል ይባርከን።

ዘላለም መንግሥቱ © 2013 (፪ሺህ፭) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት




ከሁለት ዓመታት በፊት በሳን ሆዜ፥ ካሊፎርኒያ በተደረገ አንድ ኮንፈረንስ ላይ ሳለሁ አንድ ስብከት አደመጥሁ። የሰባኪው ዋና አሳብ ያ ባይሆንም ትልቅ የስብከቱን ክፍል ገምሶ የወሰደው፥ *እናንተ ኢትዮጵያውያን ፈላሻዎችን በማሰቃየታችሁ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላችሁ ንስሐ ግቡ፤ ሕዝባችሁን ወከላችሁ ተናዘዙ፥ እርግማን አለባችሁና፥ አብርሃምን የረገሙ የተረገሙ ናቸውና ንስሐ ግቡ* የሚል ነው። ቃል በቃል ባይሆንም አሳቡ ይህ ነው።

ወዲያውኑ ሁለት ትልልቅ ጥያቄዎች ተፈጠሩብኝ። <u>አንደኛው</u> ሰባኪው አበሻ ሳለ እንዴት ነው 'እናንተ ኢትዮጵያውያን' እያለ የሚናገረው ራሱን ከዚያ ነጥሎ ብዬ ስመራመር አቆየኝ። (ትንሽ ዘግይቼ ትውውቁ መጨረሻ ላይ ነበር የገባሁት።) ኋላና ከስብከቱም ስረዳው ጥንት ፈላሻ ኋላ ቤተ እስራኤል ከሚባሉት ወገን ነው። ከዚህ ጋር የተያያዘው ጥያቄዬ፥ ለመሆኑ ፈላሻዎች እነማን ለመሆናቸው የአማካዩ ክርስቲያን ግንዛቤ ምን ያህል ነው? የሚል ነው። <u>ሁለተኛው</u> ጥያቄዬ የሚሰበከው ለክርስቲያኖች ሆኖ ለምንድር ነው ዳግም የተወለዱ፥ ክርስቶስን የተቀበሉ፥ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ሰዎች የአብርሃም እርግማን የሚኖርባቸው? ለመሆኑ ሰባኪውም ክርስቲያኖቹም የእርግማንን እና የንስሐን ምንነት በውል ተረድተዋል? የሚል ነበር።

ሰውየው ለምን ራባይ እንደተባለ ባልረዳም ራባይ ብሎ ነው ስለራሱ የሚናገረው። 'ራባይ' ፈረንጆቹ የሚጠሩት ዘዬ ሆኖ የቤተ ክርስቲያን ሳይሆን የአይሁድ ምኩራብ አገልጋይ ነው። በአማርኛውና በአራማይስጡ አጠራር ረቢ የሚባለው ሆኖ ሳለ ለአማርኛው ተናጋሪ ሕዝብ ለምን እንዲያ እንዳልተሰኘ ግልጽ አይደለም? ይህ ሰው የአይሁድ ምኩራብ ረቢ ነው ወይስ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ? ራሱን ሁለቱንም ስላደረገ ቅይጡ ለመለየት አስቸጋሪ ነው። ብቻ በስብከቱ በአጠቃላይ በኢትዮጵያውያን ሁሉ ላይ፥ በተለይም እዚያ በተሰበሰቡት ክርስቲያኖች ሁሉ ላይ እርግማንን ቆለለ። ራሱን ተሰዳጅ እኛን አሳዳጅ፥ እና በማሳደዳችን ምክንያትም የተረገምን አደረገን። *በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም* የሚለው ቀረና በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትም ጉባኤተኞች በጅምላ ተኮነኑ። በክርስቶስ በኩል ይቅር ተብለው የእግዚአብሔር ልጅ እንዳልሆኑ ሁሉ፥ ምዕመናኑም እግዚአ ይቅር በለን ብለው ተደፉ። የተሰበረ መንፈስ መልካም ቢሆንም በመንፈስ ቅዱስ የተሰበረ መንፈስና በሰው እጅ የተከሰከሰ መንፈስ የተለያዩ መሆናቸው መረሳት የለበትም። ይህ አጭር መጣጥፍ ከላይ ባቀረብኳቸው ፈላሻዎች እነማን ናቸው? እና እርግማን ምንድር ነው? በሚሉ ሁለት ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር ነው።

## እርግማን?

በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ ሌላ፥ "አይሁድን ስለበደላችሁ ንስሐ ግቡ" የሚል የአይሁዳውያንና የክርስቲያኖች ቡድን በኢትዮጵያ ተገኝቶ በአዲስ አበባ የወር ጸም ጸሎት ተደርጎ ነበር። አብርሃምን የረገመ እርግማን አለበት፤ "የአብርሃምን ዘር ረግማችኋል፤ አሰቃይታችኋልና ንስሐ ግቡ" የሚል ነው ጥሪው። እርግማኑ አበሾች ፈላሾችን ማሳደዳቸውን የተመለከተ ነው። አሳቡ ፈላሾች የአብርሃም ልጆች ናቸውና እነርሱን ማሳደድ አብርሃምን ማሳደድ ነውና ይህ እርግማን ነው የሚል ነው። ይህንን ለጥጠን ከወሰድነው እስማዔልም ዔሳውም ዐረቦችም ሁሉ የአብርሃም ዘር ስለሆኑ በአንድ ወቅት ወይም በሌላ በሌሎች ወገኖችም ሆነ በእስራኤልና በእስራኤላውያንም ጭምር በደል ደርሶባቸዋልና እስራኤልም ንስሐ መግባት ሊኖርባት ነው። ንስሐ ለሚያስገቡቱ አይሁዳውያን ሰዎች ይህ የሚዋጥ ነገር አለመሆኑ ግልጽ ነው። እርግማንን በተመለከተ በጣም የተቆላመሙና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ትምህርቶች ይሰማሉ።

"እኛ ጥቁሮች የኩሽ ልጆች የተረገምን ሰዎች ነን" የሚል የደኸየ አመለካከት ያላቸው አሉ። እነዚህ ሰዎች ሌሎች የሚጭኑባቸውን የባርነት ስነ ልቡና ጭነት ለመሸከም ትከሻቸውን ዝቅ ዝቅ የሚያደርጉ ስነፎች ናቸው። በጥቁሮች የባርነት ዘመናትና የባሪያ ንግድ በደራባቸው ዘመናት አንዳንድ ስግብግብነት፥ ዘረኝነት፥ ትምክህተኝነትና ክህደት የተጠናወታቸው ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስም በመጥቀስ ጥቁሮች (ኩሾች) ለባርነት የተዳረጉ መሆናቸውን ሳያፍሩ ይሰብኩ ነበር። በአፍ የሚናገሩትን ክፍለ ምንባብ በስፍራው በጥሞና ቢያነቡት ከነዓን እንጂ ኩሽ አለመረገሙን ለመረዳት አይሳናቸውም ነበር። የቁርበት ጥቁረትም ከባርነት ጋር የተቆራኘ አለመሆኑን ማወቅ ይችሉ ነበር። "እናንተ ጥቁሮች የተረገማችሁ ናችሁ" የሚል መጽሐፍ ያላቸውም አሉ። ለምሳሌ፥ የሞርመኖች መጽሐፍ ጥቁርነትን የእርግማን ምልክትና ውጤት አድርጎ ያስተምራል፤ 2Nephi 5:21፤ Alma 3:6-9፤ Mormon 5:15፤ Pearl of Great Price ከሚለው መጽሐፋቸው ደግሞ Moses 7:8-22። (በአማርኛ የመጽሐፎቹን ስሞች አላውቅምና ነው ጥቅሶቹን በእንግሊዝኛው ያስቀመጥኩት።) ይህን አሳብ ሕዝብንና እርግማንን ለማያያዝ ያህል አቀረብኩት እንጂ ከላይኛው አሳብ ጋር የተቆራኘ አይደለም።

"የተረገማችሁ ሰዎች እርግማን ያለባችሁ እርግማኑን እንስበር" የሚል ጥሪ አንቱ ከሚሰኙ ቱባ ሰባኪዎቻችንም ተደጋግሞ ተደምጦአል። ይህ እርግማን የአያቶችና የቅድመ አያቶች ወይም የማኅበረሰብ ሊሆን ይችላል። እርግማን በግለ ሰብ ወይም በቤተ ሰብ ወይም በማኅበረ ሰብ ላይ ሊጣበቅ የሚችል መሆኑ እውነት ነው። እርግማን በአጭር ቃል ለተደረገ ግፍና ጡር የሚመለስ ምላሽ ነው። የኃጢአት ቅጣት ነው። እርግማን ይህ ከሆነ እውነት በጌታ የዳንን አማኞች በፈላሻዎች ምክንያት ወይም በሌላ እርግማን አለብን ወይ? ረጋሚው ማን ነው? ተረጋሚውስ? ምክንያቱስ?

አንድ ሰው በክርስቶስ ሲሆን እኮ ለውጡ እስከ ፍጥረቱ ድረስ ነው፤ አዲስ ፍጥረት ነው የሆነው። ክርስቲያን ይህንን አዲስ ማንነቱን፥ አዲስ መታወቂያውን፥ አዲስ ስፍራውን ካልተረዳ ለቀጣዩ ክርስቲያናዊ እድገት እንቅፋት ይሆንበትና ታኮ እንደተደረገበት የጭነት መኪና ይሆናል። ክርስቲያኖች ከኩነኔና ከእርግማን ነጻ መውጣታችንን ካላስተዋልን የስነ ልቡና እስረኞች ሆነን እንኖራለን። ይህ ደግሞ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሆነውንና ያደረገውን ከግምት በታች ማድረጋችን ነው።

በዚህ ጉዳይ ላይ የእርግማን ቀውስ በሚል ርእስ ከዚህ በፊት (ዕዝራ #12 ላይ) ጽፌአለሁ በስፋት ለመቃኘት ያንን መመልከት ይቻላል። ይህ እርግማን በክርስቶስ ያገኘነውን ማንነታችንን ካልተገነዘብን ከመራመድ

የሚገታ እንቅፋት ይሆንብናል። በፍርሃት ወጥመድ ተከብበን እንድንኖር ያደርገናል። በእያንዳንዱ እርምጃችን በመሳቀቅ እንድንመላለስ ያደርገናል። በተለምዶና በባህላችን እርግማን የሚባለው ነገር በሰዎች ላይ መጥፎ ነገር እንዲደርስ ሰዎች የሚያሳቅሉት፥ ለታቦታት የሚሳሉት፥ ለጠንቋይና ለባለዛሮች ገብረው የሚማጠኑት ሰይጣናዊ አሠራር ነው። በዚህ ሳቢያ የሚከሰቱ መጥፎ ነገሮች (የአካል ጉዳት፥ የትዳር መፍረስ፥ የንብረት ውድመት፥ ወዘተ) ኢጋንንታዊ አሠራሮች ናቸው። ክርስቲያን በክርስቶስ አምኖ ሲድን እነዚህን ነገሮች የማያደርግም፥ በክርስቶስ ደም ተሸፍኖልና የነዚህ ነገሮች ሰለባም የማይሆን ፍጡር ሆኖአል። ይህ እውነት ነው። ይህንን ከልብ ካልተረዳን መከረኞች ሆነን እንኖራለን።

በቀደመው አባታችን በአዳምማ ሁላችንም ተኮንነናል፤ በክርስቶስ ግን ጸጋው አጽድቆናል፤ ሮሜ. 5፥15-21። ስለዚህ ከክርስቶስ ውጪ ያለ ማንም ሰው ከእርግማን በታች ነው። አዲስ ኪዳን እርግማን የሚለው ይህንን በብሉይ ኪዳንን ሕግ ሥራ ጸንቶ አለመቆምን ነው፤ ገላ. 3፥10-13። ማንም ሰው ወደ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ግን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ይህንን እርግማን ስለሻረው ነጻ ሆኖአል፤ *በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጅን*፤ ገላ. 3፥13።

አንድ ክርስቲያን ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ስላደረጋቸው ግፎችና በደሎች ሁሉ በተገቢው ሁኔታ መናዘዝና ንስሐ መግባት አለበት። ግለ ሰቦችን ከበደለ ግለ ሰቦችን ይቅርታ መጠየቅ፥ ሕዝብን ከበደለ ለሕዝብ መናዘዝ፥ የሚጠየቅበትና የሚፈረድበት፥ ገንዘብ መመለስና መክፈል ወይም ቅጣት መቀበል የሚገባው ነገር ከኖረም ያንን ማድረግ ይጠበቅበታል። ተሸፋፍኖ መሸሽ የለበትም። ክርስትና ዘላለማዊ ቅጣታችንን የተቀበለልንን ጌታ ተቀብሎ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን እንጂ ቀድሞ ካጠፋነው ጥፋት ቅጣት ለመሸሽ መደበቂያ አይደለም። ያ በመደበቅ ሳይሆን በመጸጸትና በመናዘዝ የምናጠፋው ነው። ከክርስቶስ እምነታችን በፊት አውቀን ከሠራነው ጥፋትና ወንጀል፥ በደልና ኃጢአት መናዘዝና መጥራት ተገቢ ነው። ከክርስቶስ ወዲህ ሌሎች በሰይጣን አማካይነት በኛ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ነገር አለመኖሩንም ማወቅ ተገቢ ነው።

አንዴ ስለዚህ ጉዳይ ስናገር አንድ ወንድም ዳን. 9ን በመጥቀስ ዳንኤል የውክልና ጸሎት እንደጸለየ እኛም ስለሌሎች መናዘዝ እንችላለን የሚል ጥያቄ አንስቶ ተከራከረ። ስለሌሎች መማለድና መጸለይ እንችላለን፤ ለመወከል ግን በመወከል ስፍራ ላይ መገኘት ይገባናል። ዳንኤል ሕዝቡን ወክሎ ቢጸልይ ስፍራው መብቱን ይሰጠዋል፤ ምክንያቱም እርሱ ከነገሥታቱና ከመሳፍንቱ ወገን ተማርኮ የሄደ ሰው ነው። በጊዜው ንጉሥ አለመኖሩ፥ ይልቁንም እንዲህ ያለውን የዘመኑን መቃረብና የተሰፋውን ፍጻሜ የሚያስተውል አለመኖሩ ጸሎቱን ተገቢ ያደርገዋል። አንድ ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ዐፄ ይስሐቅ ወይም ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ያደረሱት በደል ከፋይ ነኝ፥ ያ ጡር ይደርስብኛል ብሎ መስጋት የለበትም። ስለ እርግማን ይህን ካልኩ በኋላ ፈላሻ ወደሚለው ወደ ርእሱ አሳብ ልመለስ።

## ሰዎቹ መቼ መጡ? ወይስ ሃይማኖቱ መቼ መጣ?

ፈላሻ የሚባሉ የሃይማኖት ወገኖች በአገራችን እንደኖሩ እውነት ነው። እነማን ናቸው? መቼ መጡ? እንዴት መጡ? የሚለው ጥያቄ ግን መልሱ በትውፊታዊ ጭጋግ የተሸፈነ በመሆኑ ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር የሚቆራኙት የታሪክ ሊቃውንት እንደሚጠይቁት፥ ሰዎቹ መቼ መጡ? ሳይሆን ይህ የአይሁድ እምነት መቼ መጣ? እንዴት መጣ? ብለን ነው መጠየቅ ያለብን። የኔም ጥያቄ ይህ ነው።

ምንጩ በትውፊታዊ ጭጋግ የተሸፈነ ቢሆንም እምነቱ ሳይሆን ሰዎቹ መጡ የሚሉት ከሚያቀርቧቸው ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. አይሁድ በግብጽ በነበሩበት ዘመናትና በአርነታቸው ወቅት ወደ ደቡብ ግብጽና ጥንት ኤለፈንታይን ወደሚባለው አካባቢ መጥተው ኖረው ኋላ ወደ ደጋው ኢትዮጵያ ተጎዳኙ።

2. አይሁድ በተበተኑባቸው በሦስቱ ታላላቅ ወረራዎች ዘመናት፥ ማለትም፥ በአሦር፥ በባቢሎን፥ እና በሮም ወረራዎች ጊዜ የተፈናቀሉትና የተበተኑት በዓለሙ ሁሉ ፊት ሲበተኑ እስከ ኢትዮጵያም መጡ።

3. በንግድና በተለያዩ ፖለቲካዊ፥ ማኅበራዊና ሌሎችም ምክንያቶች ከዐረብ አገር ቀይ ባሕርን ተሻግረው በተለያዩ ጊዜያት መጡ።

4. በክብረ ነገሥት የተዘገበው የንጉሥ ሰሎሞንና የንግሥተ ሳባ ታሪክ።

## ክብረ ነገሥት

የሰሎሞንና የሳባ ንግሥት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኝ ቢሆንም የኛው ክብረ ነገሥት ታሪክ ምንጩና መነሻ ምክንያቱ ከተጻፈበት ዘመን ጋር የሚቆራኝ ነው። ታሪኩ ንግሥተ ሳባ ከንጉሥ ሰሎሞን አርግዛ መመለሷን፥ ልጇ ምኒልክ እዚህ መወለዱን፥ ለአቅመ አዳም ሲደርስ አባቱን ሊያይ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱን፥ ወደ አባቱ ሄዶ ሲመለስ ታቦቱን ሰርቆ፥ አብረውት 12 ሺህ አይሁድ አጅበውት፥ መልአኩ ሚካኤል እየመራቸው በደማቅ ሰልፍ ወጥተው መምጣታቸውን ወዘተ፥ ይተርካል። የአመጣጣቸው ጉዞ ትንግርታዊ ነው።

ለፈላሻዎች በኢትዮጵያ መገኘት እንደ ዋና ምንጭ የሚጠቀሰው አገራዊው ሰነድ ይህ ነው። የዘመኑ ዳራ ሲጠና ስርወ መንግሥቱ በጊዜው አገሪቱን ይገዛ ከነበረው ከዛጔ እጅ 'ሰሎሞናዊ' ተብሎ ወደተጠራው እጅ እንዲገባ የተቀናበረ ጽሑፍ መሆኑ በግልጽ ይታያል። ይህ ታሪክ የተሠራው/የተተረጎመው በ13ኛው ምዕት ዓመት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ሆኖ ሳለ ታሪኩም ሰነዱም ቀድሞ በኢትዮጵያ አለመገኘቱና ከግብጽ፥ ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ መተርጎሙ ሥራውን የጥያቄ ማጥ ውስጥ ይከትተዋል። ስለ ተአምረ ማርያም በዕዝራ #16 የተነተነው የምንጭ ሙገታም ከዚህ ይመሳሰላል። ተአምረ ማርያም በኢትዮጵያ ደብሮችና አውራጃዎች የተደረጉ ተአምራት መድበል ሆኖ በኢትዮጵያ ሳይሆን በግብጽ ተጽፎ ወደ ግዕዝ እንደተተረጎመው ማለት ነው።

ይሁን፤ ብዙ ሺህ አይሁድ በመጽሐፉ (በክብረ ነገሥት) ውስጥ እንደተጻፈው ባለ ደማቅ ታሪክ ታጅበው መጡና ኖሩ ቢባል፥ ደግሞም እንደተተረከው ቀድሞ የሳባ ንግሥት፥ ኋላም የሰሎሞንና የሳባ ንግሥት ልጅ የሆነው ምኒልክ የአይሁድን ሃይማኖት ተቀብሎ መጣ ቢባል ከዚህ ጋር የሚጣሉ ሞጋች ጥያቄዎች ይነሣሉ።

አንደኛው፥ ንጉሡ ምኒልክም፥ እናቱም ንግሥተ ሳባ የአይሁድን እምነት ተቀብለው በእስራኤል አምላክ አምነው ከመጡ ከክርስትና እምነት በፊት የአይሁድ ሃይማኖት የአገሪቱ ሃይማኖት ሆኖ መገኘት ነበረበት። በተለይ 12 ሺህ አይሁድ ከመጡ ይህ ይህ ሃይማኖቱን ብቻ ሳይሆን ቋንቋውንና

ባህሉን፥ ጽሑፉንም ጭምር የሚያንሰራፋ ፍልሰት ነውና ቋንቋቸው መግነን፥ ፊደላቸውና መጽሐፋቸውም መሰራጨት፥ ባህላቸውና ወጋቸውም መናኘት ነበረበት። ነገር ግን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እስከ ክርስትና መምጣት ድረስ የአገሪቱ አማልክት ሰማይና ምድር፥ ዘንዶና ባሕር ነበሩ እንጂ የእስራኤል አምላክ አልነበረም። በታወቀው በአክሱም ሥልጣኔ ዘመን የነበረውም ይኸው ነበር። የነገሥታቱ ሐውልቶችና የዘመኑ ገንዘብ ማኅተሞች የሚያሳዩትም ይህን ነው። በቁፋሮ ከተገኙ ማስረጃዎች የብሉይ ኪዳን እምነትን መኖር ያመለከተ ቅርስ ከቶም አልኖረም። እንግዲህ ነገሥታቱ ሰሎሞናውያን ሆነው ከሰሎሞን ዘመን (ከ900 ዓ. ዓ.) ጀምሮ እስከ ክብረ ነገሥት ድርሰት (1270ዎቹ ዓ. ም.) ቅንጣትም ሰሎሞናዊ ምልክት ከሌለ ምን ይባላል?

ሁለተኛው ግጭት ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ክብረ ነገሥትና የቀዳማዊ ምኒልክ ታሪክ ሲፈተሽ ያለው ትልቅ ተቃርኖ ነው። አንደኛው የዓመታት ዘመናትና ዕድሜዎች ስሕተቱን (የክብረ ነገሥትን) ማጋለጡ ነው። ሰሎሞን መቅደሱን ሲያሠራ በነገሠ በ4ኛው ዓመት ተጀምሮ በ7 ዓመት ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን የተፈጸመው በነገሠ በ11ኛው ዓመት ነው፤ 1ነገ. 6። የራሱ ቤተ መንግሥት ደግሞ 13 ዓመት ፈጅቶ በነገሠ በ20 ዓመቱ ተጠናቀቀ፤ 1ነገ. 7 እና 2ዜና 8። ንግሥተ ሳባ ወደ ሰሎሞን የሄደችበት ታሪክ የተጻፈው በ2ዜና 9 መሆኑ በቅደም ተከተሉ መሠረትና ያየችውን ከማድነቋ አንጻር ሄዳ ንጉሡን የጎበኘችው ከነዚህ 20 ዓመታት ንግሥ በኋላ ነው ማለት ነው። ሠርቶት የነበረውን ቤትና በእግዚአብሔርም ቤት የሚያሳርገውን መስዋዕት አይታ አድንቃለች። የሳባ ንግሥት ልክ በ20ኛ ዓመቱ እንኳ ሄደች ቢባልና ያኔውኑ አርግዛ ተመለሰች ቢባል በ21ኛ ዓመቱ ወልዳለች ማለት ነው። ክብረ ነገሥት ደግሞ በምዕራፍ 33፥10 ምኒልክ በ22 ዓመቱ ገና ውጊያ፥ የፈረስ ግልቢያና አደን ሲማር እንደነበረ ይነግረናል። ምኒልክ በዚያው ዓመት (በ22 ዓመት ዕድሜው) ቢሄድ እንኳ በሰሎሞን 43ኛ ዓመተ መንግሥት ደረሰ ማለት ነው። ሰሎሞን በዚህ ጊዜ ከነገሠ 29 ዓመቱ ብቻ መሆኑን ይናገራል (ከ.ነ. 37፥6) ምኒልክም በነገሠ በ7ኛው ዓመቱ የተወለደ የበኩር ልጁ መሆኑንም ያወሳል፤ ሮብዓም ከሰሎሞን በኋላ ሲነግሥ የ41 ዓመት ሰው መሆኑ ሰሎሞን ገና ሳይነግሥ የወለደው ልጁ መሆኑን ያሳያል እንጂ ምኒልክን በኩሬ ሊለው አይችልም፤ 1ነገ. 14፥21። ይህ በግጭት ውስጥ ያለ ሌላ ግጭት ሆኖ ወደ ዋናው ግጭት ስንመለስ ምኒልክ በሰሎሞን በ20ኛው ዓመት ተረግዞ በ21ኛው ዓመት ተወልዶ በ43ኛው ዓመት ሊነበኘው ሄዶ (በ22 ዓመት ዕድሜው) 3 ዓመት ቆይቶ በ46ኛው የሰሎሞን ዓመተ ንግሥ ተመለሰ ማለት ነው። ግጭቱ እንግዲህ ሰሎሞን 40 ዓመት ብቻ መንገሡ ነው።

ሦስተኛው ትልቅ ግጭት በሮብዓም የልጅ ልጅ በአሳ ዘመን ኢትዮጵያዊው ዝሪ ይሁዳን ሊወጋ ሚሊዮን ሠራዊት ይዞ መውጣቱና ሠራዊቱ ሁሉ ተመትተው መውደማቸው ነው። ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከሆነ ዝሪ ምናልባት ልጁ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም አሳ ሲነግሥ ሰሎሞን ከሞተ 40 ዓመትም አልሞላም (ሮብዓምና አብያ 17፥17 ዓመት ነው የነገሡት)። ምናልባት ዝሪ የተባለው ራሱ ምኒልክም ቢሆንስ? አሳ ሲነግሥ ምኒልክ ገና በዕድሜ 60ዎቹ አጋማሽ ቢሆን ነው። አጭር የሠርግና ምላሽና የጫጉላ ዘመኑ አልቆ ተረሳና ጦርነትና ወረራ ማሰለፉ ምነው በኛው ታሪክ ተዘለለ? ወይስ ሌላ ኢትዮጵያ፥ ሌላ ኩሽ ነው ወራሪው? ይህ ታሪኩ መዘለሉን ሳይሆን የክብረ ነገሥቱ ትውፊት ከቶም ያልነበረና ለምክንያት የተፈጠረ መሆኑን የሚያስረዳ ሌላ ጠቋሚ ነው። ስለዚህ በአጭር ቃል፥ በዚያ ዘመን የመጡ አይሁድና ከእነዚያ የተወለዱ ፈላሻዎች የሉም ማለት ነው። ስለዚህ አይሁድ መቼ መጡ ከማለት ይልቅ ሃይማኖቱ መች መጣ ማለቱን እንመልከት።

## የአይሁድ እምነት መቼና እንዴት መጣ?

የአይሁድ እምነት መቼ መጣ? እንዴት መጣ? የሚለው ተገቢ አጠያየቅ መሆኑ ተወስቶአል። ሰዎቹ በገፍ ሳይሆኑ እምነቱ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች መምጣቱን የፈላሻዎች (ቤተ እስራኤል) በአገሪቱ መኖር ብቻውንም ይመሰክራል። የሰዎቹ ከሃይማኖቱ ጋር ተቆራኝቶ መኖር ራሱን የቻለ የእምነቱ ምስክር ነው። ሃይማኖቶች በዘመናት መካከል ሲስፋፉና ሲዛመቱ ኖረዋል። በሰላማዊ መንገድ ሃይማኖታዊ ሐዋርያነትም ግየራም ያለ ነው። ሰዎች ወደ ይሁዲነት በተለያዩ አጋጣሚዎች በነጠላም በወልም ሲገየሩ ኖረዋል። በነጠላ እንደ ሞዓባዊቱ ሩት የመሰሉት ወደው ከሕዝቡ ጋር ዕድል ፈንታቸውን አድርገዋል። በጅምላ አይሁድ ከሆኑት ለምሳሌ፥ በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ ሐማ ከሞተ፥ መርዶክዮስ ከተሾመና አይሁድ ሊፈጁበት የነበረው አዋጅ ከተገለበጠ በኋላ ብዙ አሕዛብ ከአይሁድ ፍርሃት የተነሣ አይሁድ እንደሆኑ ተጽፎአል፤ አስ. 8፥17። የዚህች የአስቴር ባል የሆነው የንጉሥ አርጤክስስ መንግሥቱ ከሕንድ እስከ ኢትዮጵያ መዘርጋቱም ተጽፎአል። መንግሥቱ እዚህ ድረስ ከተዘረጋች ሃይማኖታዊ ተጋቦቱም ሊኖር ቢችል አያስደንቅም።

የአይሁድ እምነት በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችም የተስፋፋ እምነት ነውና እምነቱ ከመካከለኛው ምሥራቅ በቀይ ባሕር ወደ ኢትዮጵያ ደጋማ ክልል ቢደርስ አስገራሚ አይደለም። ከባሕሩ ወዲህና ወዲያ ማዶ ግንኙነትም ጣምራ አገዛዝም ኖሮ ያውቃል። እምነቱ ከውጭ የመጣ ብቻ ሳይሆን ከውስጥ ከክርስትና ተፈንቅሎ የወጣ ልምምድም ሊሆን ይችላል። በኢትዮጵያ ከአመጋገብ እስከ አለባበስ፥ ከሰንበት እስከ ታቦት የአይሁድ ባህል የነነበትና የብሉይ ኪዳን ድባብ ያጠላበት ክርስትና በታሪክ ውስጥ መኖሩ ይህ የፈላሻዎች ሃይማኖት ከውጭ የመምጣቱን ያህል ከውስጥ የመውጣቱም ነገር ከግምት ማስገባት ይችላል።

ፈላሻዎች በኢትዮጵያ መኖራቸው ከክርስትና በፊትም ሆነ ከክርስትና ወደ አገሪቱ መግባት ጀምሮ ክብረ ነገሥት እስከተጻፈበት ዘመን ከሺህ ዓመታት በላይ አይታወቅም። ያኔም ታሪኩ ተጻፈ እንጂ ፈላሻዎች እንደ ሕዝብ ወገን ወይም እንደ ነገድ መኖራቸው አልተዘገበም። በ9ኛው መቶ ተዓማኒነቱና አጠያያቂ የሆነ ኤልዳድ ሐዳኒ (የዳን ተወላጁ ኤልዳድ) የተባለ አይሁዳዊ ነጋዴ ተጓዥ ሰው በጉዞ ታሪኩ በዓባይ ወንዝ ዳርቻዎች የተለያዩ የአይሁድ ነገዶችን ማግኘቱን ይተርካል። እነዚህ ነገዶች ከኢትዮጵያ ነገሥታት ጋር ይዋጉ እንደነበርም ተርኳል። እንደ ኤልዳድ አባባል የዓባይ ዳርቻ አይሁድ የዳን ልጆች ናቸው። ይህ ኤልዳድ የዳን ልጆች ስለሚላቸው ስለ ፈላሻዎች ጻፈ የሚል ግምት ያላቸው አሉ፤ የታሪክ ጠበብት ግን በግምት የተጻፈ ነው ይላሉ። ይህ አይሁዳውያን የታሪክ ሊቃውንትንም ይጨምራል።[1] ከዚያ ጊዜ በኋላና ከዚህም ተያይዞ የቁሱ የሐንስ አገር በሕንድ ወይም በአፍሪቃ ውስጥ አገር መኖሩና ይህ ሃይማኖታዊ ንጉሥ ገናናና ቀናዒ መሆኑ ናኘ። የአውሮጳ ክርስቲያኖች ቅድስት አገርን ከሙስሊሞች መዳፍ ነጻ ለማውጣት የመስቀል ጦርነት

[1] *Jewish Quarterly Review, Vol. 17. 1926-27*

ያሉትን ያወጁበት ጊዜ በመሆኑ ከዚህ ጋር ተቆራኝቶ ቄስ ንጉሥና የአይሁድ ሕዝብ መገኘት ትልቅ ኢጋር በመሆኑ ታሪኩ ተወዳጅ ሆነ።

## ፈላሻ፥ ፈላሲ?

ፈላሻዎች ከዚያ ከ13ኛው መቶ ምዕት ዓመት በኋላ ግን በነገሥታቱ ዜና መዋዕል ውስጥ የተጠቀሱባቸው ጊዜዎች አሉ። ሰሎሞናዊ ከተሰኘው ስርወ መንግሥት ቀደም ያለው የዮዲት ወረራና የዛጔ መንግሥት ፈላሻዊ ሳይሆን አገዋዊ መሆኑን የታሪክ ጸሐፍት ይስማማሉ። ዛጔ የሚለው ቃልም 'ዘአገዉ' መሆኑን የቋንቋ ጠበብት ያወሳሉ። ከ13ኛው መቶ በኋለኞቹ ነገሥታት ዘመናት ግን ነገሥታቱ ኃይማኖትን የፖለቲካ መሣሪያ ለማድረግም ሕዝቡን አንድ መልክ ለማስያዝ ይጥሩ ነበርና ግጭቶች ኖረው ክርስትናን ያልተቀበሉት ወገኖች ፈላሲ ይሁኑ ተብሎ ተፈርዶባቸው ኖረዋል። ይህ የፈላሲነት ውግዘት ከተከታታይ ዓመጾች በኋላ የታወጀ ስልታዊ የቅጣት አዋጅ ነው። በዐፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት 1413-30 ነው ይህ የተጠና ማዕቀብ የተጣለባቸው። እነዚህ ሰዎች እንደ ከሐዲ በመቆጠር ወደ ክርስትና እንዲመጡ ታወጀ። ከአዋጁ ቃል፥ "በክርስትና ሃይማኖት የሚጠመቅ ሁሉ የአባቱን መሬት ይወርሳል፤ ያለዚያ ግን ፈላሲ ይሁን" የሚል ይገኝበታል።[2] ከዚያ በኋላ ይመስላል ይህ ፈላሲ፥ ፈላሻ የሚል ቃል መለመድ የተጀመረው። ከዚህ አዋጅ የምንረዳው ፈላሻዎች ፈልሰው የመጡ ሳይሆኑ ክርስቲያን ባለመሆን የተፈናቀሉ ሰዎች መሆናቸውን ነው።

## ዓይን አይቶ ምን ይፈርዳል?

ከላይ እንደተጠቀሰው የዕብራዊ ቋንቋና ጽሑፍ በኢትዮጵያ መኖሩ በታሪክም አይታወቅም። የፈላሻዎች ቋንቋ የአገሬው (የቋራ፥ የቄይላ፥ የአገው፥ ኋላ የአማርኛ) ቋንቋ ነው። መጽሐፋቸውና ቅዳሴያቸውም ጭምር የግዕዝ እንጂ የዕብራይስጥ አለመሆኑ ፈላሻዎች ፈልሰው የመጡ የራሳቸውን ቋንቋና ቅዱሳት መጻሕፍት ይዘው የተሰደዱ ያለመሆናቸውን ያሳያል። ግዕዝም ራሱ ከሳባ ቋንቋ የቀጠለ ደኃራዊ ቋንቋ ነው።

አገሬ መሆናቸውን የሚያረጋግጠው ሌላ ግልጽ ነገር መልካቸው የአገሬው መሆኑ ነው። ስለዚህ ነው የአይሁድን እምነት የተቀበሉ የጥንት የአገው ሰዎች ናቸው እንጂ ከባሕር ማዶ የመጡ ከቶም አይደሉም ብለው የታሪክ ሊቃውንት የሚጽፉት። ፈላሻዎች በኖሩባቸው አካባቢዎች ከሰሜን ጣና እስከ ሰሜን ጎንደር ባለው ክልል የእነርሱና የነዋሪው መልክ ምንም ልዩነት ያለው አይደለም። ተደርድረው ቢቆሙ ባሩኽን ከብሩክ ወይም ሞሼን ከሙሴ መለየት አይቻለንም። ለነገሩ የቋንቋ ልዩነት ስላልነበረ በመልክ ብቻ ሳይሆን በስምም ልዩነት አልነበረም። ከቅርብ ዓመታት በኋላ የአይሁዳዊነት ስሜት ሲያይል ከተፈጠሩ ስያሜዎች ሌላ ስማቸውም ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ የአገሬው ነው። ለውጥ የለም።

ፈላሻዎች በ3 ዙር የተቀናበሩ ዘመቻዎች፥ በዘመቻ ሙሴና ኢያሱ በሱዳን በኩል ከተደረገው ሌላ በዘመቻ ሰሎሞን በደርግ መፍረስና በኢሕአዴግ መግቢያ ቀናት ውስጥ በተደረገው የጅምላ ጉዞ የመልክ መመሳሰል ስላለ የላም በረትና የመገናኛ አካባቢ ወጣቶችና መንገደኞችም ጭምር እየተቀላቀሉ በአንበሳ አውቶቢስ እየተሳፈሩ ወደ አውሮፕላን ጣቢያ የሄዱበትና ወደ እስራኤልም የበረሩበት አጋጣሚ ነበረ። ይህ ለአንዳንዶች ከ3ኛው ዓለም ወደ 1ኛው በቀጥታ የመግቢያ አቋራጭ ቶምቦላ ነውና ቆርጠውት ሄደውበታል። ለምሳሌ፥ በMarch 1991 በቢቢሲ በተዘገበ አንድ ዘገባ በዚያ ሰሞን ከሄዱት 2228 ተጓጉች 350ው ብቻ ፈላሻ መሆናቸውን አንድ የእስራኤል ኤምባሲ ዲፕሎማት መዘገቡን ጠቅሶአል።[3] እስከዚህ ድረስ ነው የመልክ መመሳሰል ማንነትን የሚጠቁመውና ለስሕተትም የሚዳርገው።

በአማካይ የእስራኤላዊ መልክ ምን እንደሚመስል ይታወቃል። ኑሮና የአየር ጠባይ፥ የዘመን ርቀትና እንግልት በመልክ ላይ ለውጥ ሊያስከትሉ ቢችሉም አበሻ ካልሆኑ በቀር ይህን የሚያህል ከአይሁድ ይልቅ ከአበሻ የሚያጣብቅ የመልክ መመሳሰል ሊመጣ አይችልም። በመልክ የምናውቃቸውን ናሙና የእስራኤል መሪዎች ከፈላሻዎች መልክ ጋር ብናነጻጽር ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳልና በመሐል ያሉት የፈላሻ ካህናት የመጀመሪያው ረድፍ ላይ ያሉትን አይሁድ ወይስ የታችኞቹን አበሾች ይመስላሉ?



## ዘመናዊ ምርመራስ?

የመልክ ንፅርን ያቀረብኩት በግምት ብቻ እንድንመልስ አይደለም። ከላይ ከቁርበት መልክ ወደ ውስጥ ማንነት እንድናልፍ ነው። የሞርመኖች ሃይማኖትና መጽሐፍ የሰሜን አሜሪካ ሕንዳውያን (Native Americans) አይሁድ መሆናቸውን መሥራቻቸው ስለጻፈ ይህን እውነት አድርገው ይቀበሉታል። ኋላ ግን በDNA ምርመራ የአሜሪካ ሕንዳውያን ዝርያ ከእስያ እንጂ ከጠፉት 10ሩ የአይሁድ ነገዶች አለመሆኑ የተረጋገጠ

[2] ታደሰ ታምራት፥ ገጽ 200-201

[3] http://www.biyokulule.com/view_content.php?articleid=2491.

ሆነ።[4] ይህ ጥናት የአሜሪካ ሕንዳውያኑ 99% እስያዊ መሆናቸውንና የመካከለኛው ምሥራቅ ዝርያነታቸው ቅንጣት እንኳ የሌለበት 0% መሆኑን ያትታል።

ፈላሻዎችን በተመለከተም የDNA ምርመራ በተለያዩ ሳይንሳዊ ላብራቷሮች ተደርጎአል። በ1999 ሉኮት እና ስሜትስ በተባሉ ሊቃውንት የተደረገ የመጀመሪያው 38 በእስራኤል የነበሩ ፈላሻዎችን (ቤተ እስራኤሎችን) ከ104 በአካባቢው የነበሩ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ያነጻጸረው የDNA ምርመራ ቤተ እስራኤሎች መመሳሰላቸው ከአካባቢው አይሁዳውያን ሳይሆን አይሁዳዊ ካልሆኑት ኢትዮጵያውያን ጋር መሆኑን አረጋገጠ። በተመሳሳይ ጊዜ በተነጣይ የተደረገ ሌላ ምርመራ ውጤትም ከዚሁ ጋር አንድ ነው። የዚህኛው ምርምራ መደምደሚያ ቃል፥ "We conclude that the Falasha people descended from ancient inhabitants of Ethiopia who converted to Judaism." (የፈላሻ ሕዝቦች ከጥንታውያን ኢትዮጵያውያን ዝርያ የሆኑና የአይሁድን ሃይማኖት የተቀበሉ ናቸው ብለን እንደመድማለን) የሚል ነው።[5] ሌላ በ2002 የተደረገ የሞርሞኖቹን ምርመራ የመሰለ የMitochondrial DNA ምርመራ ኢትዮጵያዊዎቹ ቤተ እስራኤሎች ምንጫቸው ኢትዮጵያ መሆኑን አረጋግጦአል። በ2009 የተደረገ Autosomal DNA ምርመራም ፈላሻዎችን ኩሻውያን ያደርጋቸዋል።[6] እንደ ሳይንሳዊው ማረጋገጫ ብያኔ ከሄድን ፈላሻዎች በዜግነት እስራኤላዊ ቢሆኑም በዘርና ደም አይሁዳውያን ያለመሆናቸውን ነው።

ይህ እይታ በሳይንስ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡም ዘንድ የሚታይ እውነታ ነው። ከቀድሞም ጀምሮ ከሕዝቡና ከመሪዎች ተቀባዮች የመኖራቸውን ያህል የፈላሻዎችን አይሁድነት የማይቀበሉና ያልተቀበሉም አሉ። ፈላሻዎች እንደ ሌላው ወደ ምዕራቡ ዓለም የሚሰደድ ስደተኛ ሁሉ በገቡበት አገርና ሕዝብ መሐል የሚያልፉባቸው ውጣ ውረዶች አሉ። ከወንዙ ጋር መፍሰስ እስኪችሉ ምናልባት የአንድ ወይ የሁለት ትውልድ ዘመን ያልፋል።

## መደምደሚያ

በፈላሻዎች ላይ የደረሰ ስደት መኖሩ እውነት ነው። ይህ የማኅበራዊ፥ የፖለቲካዊውና የልማዳዊው ሃይማኖት ድርና ማግ ውጤት ነው። ሰውን በእምነቱ ማግለልና ማሳደድ ፈጽሞ ስሕተት ነው። ግን ይህንን የአሁኑን ዘመን የኅሊና ንቃትና የኅሊና ነጻነት መብት የዛሬ 500 ወይም አስር መቶ ዓመት በፊት ወደነበረው ነባራዊ ሁኔታ ወስደን መጫን አንችልም። የአይሁድ እምነት መኖር ማለት ሃይማኖቱ ሕዝቡን በትውልድና በዜግነት ደረጃ ለውጥታል ማለት አይደለም። ከሆነማ በቅርብ ስልጤዎች፥ "እኛ ዐረባውያን ነን አሉ" እንደተባለው፥ የወለጋው መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ሰው፥ "እኔ ሱይድናዊ ነኝ" ወይም የአዳባ ካቶሊክ ምእመን፥ "እኔ ደግሞ ጠሊያን ነኝ" ቢል ልክ ነው ልንል ነው። እምነትና ማንነት ለየቅል ናቸው። የአይሁድ እምነት፥ ያውም በሙሉው ሳይሆን በከፊል በኢትዮጵያ መገኘቱ የሃይማኖቱን ተከታዮች የምንጩ ሰዎች አያደርጋቸውም። ስለ ፈላሻዎች ማንነት ይህ በቂ ሆኖ የመነሻውን አሳብ እንደገና በማንሣት ልደምድም።

የመነሻው አሳብ፥ አይሁድን (ፈላሻዎችን) በድላችኋልና ንስሐ ግቡ የሚለው ነጥብ ነው። ፈላሻ የሚለውን ቃል ሰምቶ እንኳ የማያውቅን የሲዳማ ወይም የጋሞ ክርስቲያን አይሁድን በድላችኋልና ንስሐ ግቡ ማለት የንስሐን ትርጉም ንጹሕ ባልሆነ ውኃ መከለስ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች የሚያውቁት ኪዳንም፥ ሕግም፥ ክርስቶስም በሥጋ የመጡት ከአይሁድ መሆናቸውን በመረዳት ለአይሁድ ቅን አሳብ ማሰብን ነው። በመግቢያው ላይ እንዳልኩት የመሰለውን አሳብ የሚፈትሉ ሰባኪዎች አሁንም አሉ። እዚያ የጠቀስኳቸው ሰዎችም *በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም* የሚለውን ሽረው በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትንም ጉባኤተኞች በጅምላ ኮነኑ። ከነርሱ የተሳሳተ አስተምህሮ ያላነሰ የሚያሳዝነው ነገር ጉባኤዎችም ከመድረክ የሚሰሙት ሁሉ እውነት የሚመስላቸው መሆኑ ነው። አንዳንዶችማ የሚነገረውን ነገር መድረኩ ቅዱስ የሚያደርገው ነው የሚመስላቸው። አማልክት ናችሁ ሲባሉ ነን፤ ቁንጫ ናችሁ ሲባሉ ነን፤ አልታመማችሁም ሲባሉ አልታመምንም፤ የረገማችሁና የተረገማችሁ ናችሁ ሲባሉ እሺ የተረገምን ነን። ይህ ቆሮንቶሳዊና ገላትያዊ ከርሞ ጥጃነት ብቻ ሳይሆን በጌታ የሆንነውን ማንነትንም ያለማወቅ መሠረታዊ እንከንም ነው።

የማንነት ቀውስ ያለበት ሰው ሌላ ለመሆን ይገደዳል። መገደዱ ከውስጡ የመነጨ ወይም ከሌላው የተጫነበት ሊሆን ይችላል። እንደ ፈላሻዎች ዘመናት ያስቆጠረ ትውፊትና ታሪክም ሰዎቹን እውነትም አይሁዳዊ እንደሆኑ ሊያሳምን ይችላል። ማኅበራዊ ጫና የግል እኛነታችንን በማኅበራዊ እኛነታችን (collective identity) እንድንለውጥ ሊያስገድደን ይችላል። ጓደኞቻችንን ለመምሰልና የግላችንን ሳይሆን የቡድን መታወቂያ ይዘን ልንዞር እንሞክር ይሆናል። ይህ በክርስትና ውስጥም ይታያል። ከክርስቲያናዊ ቋንቋ እስከ ጸጋ ስጦታ፥ ከሕግ ጥበቃና እስከ አገልግሎት ድረስ የኛ ያልሆነ የወል ማንነት ይዘን ልናዘግም ግዴታ ውስጥ መግባት የለብንም።

ክርስቲያኖች የማንም ረጋሚዎች አይደለምሉ መሆንም የለባቸውም። ሊረግሙ ሳይሆን ሊመርቁ፥ እንዲያውም ጠላቶቻቸውንም ሳይቀር ሊባርኩና በረከትንም ሊወርሱ የተጠሩ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ናቸው። ክርስቲያኖች ክርስቶስን ሲቀበሉ ከኩነኔ ነጻ ሆነዋልና እርግማንም የለባቸውም። ከኃጢአትና ከሞት ሕግም ነጻ ወጥተዋል። እንደገና ተወልደው የእግዚአብሔር ልጆች ሆነዋል። ይቅርታ የተቀበሉ፥ ምሕረትን ያገኙ፥ ወገኑና ሕዝቡ የሆኑ፥ የእርግማን ሳይሆን የበረከቱ ተካፋዮች ሆነዋል። በክርስቶስ ስንሆን አዲስ ፍጥረት ሆነናል። አሮጌው ነገር ሁሉ አልፎ ሁሉ አዲስ ሆኖአል። ይህ በክርስቶስ ያገኘነው የከበረና የተባረከ አዲስ ማንነታችንና መታወቂያችን ነው። በክርስቶስ ስናምን በደሙ የተሸፈንን በመሆናችን በእርሱ እስከኖርን ድረስ ይህን ሽፋን የሚጥስና የሚነካን በኛ ላይ የሚወረወር መርግና ፍላጻ የለም፤ አይኖርምም። ክርስቲያኖች በክርስቶስ ያለውን ፍጹምና የሆነ አርነት በምንሰማውና በሚነገረን መለወጥ የለብንም። ሰው ራሱን ሲሆንና በዚህ ኹነቱ ሲረካ በማንነቱ መደሰት ይጀምራል። ይልቁንም በክርስቶስ ያገኘውን ዘላለማዊ ማንነት የተረዳ ሰው እርካታው ዘላቂና ዘላለማዊ ነው። ይህን ዘላለማዊ ማንነታችንን በመረዳት እንድንረካ ጌታ ይርዳን።

[4] *Losing a Lost Tribe: Native Americans, DNA, and the Mormon Church.* ጠቅላላ መጽሐፉ ላማናውያን የተሰኙት የሰሜን አሜሪካ ሕንዳውያን አይሁድ አለመሆናቸውን በሳይንሳዊ ርገድ ያረጋገጠ ነው።

[5] *http://www.ncbi.nlm.nih.gov/pubmed/10592688.*

[6] *http://en.wikipedia.org/wiki/Beta_Israel.*

ዘላለም መንግሥቱ © 2013 (ፀሸሀ፭) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት



# ደስ፣ ደስ፣ ደስ፣ ደስ

ፊልጵ ~~የምትከበት ፡ ይሆንልኛል ።~~ ነገር ፡ ግን ፡ በአ
ምነታችሁ ፡ መሥዋዕትና ፡ አገልግሎት ፡ ተጨ
ምሬ ፡ ሕያውቴ ፡ እንኳ ፡ ቢፈስ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፡
ከሁላችሁም ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፤
፲፰፤ አናንተም ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡
ክእኔም ፡ ጋር ፡ አብራችሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።

ባለፈው የፊልጵስዩስ ጥናት ከመጥፎና ጠማማ ትውልድ እንዲጠበቁ የመከራቸውን ምክር አውስተን ነበር። የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖችም ሁሉ በትውልዳቸን ውስጥ በኃላፊነት፥ ማለትም በተጠያቂነት፥ የምንታይና የሚታዘቡን በመሆን ተቀምጠናል። ተወዝፎ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን የሕይወትን ቃል እያቀረብን እንደ ብርሃን የምንታይም ነን። ሁለቱም ነን፤ የሚሰማና የሚደመጥ ቃል ያለን፥ የሚታይ ብርሃን የሚንጸባረቅብንም ነን። የሚደመጥ ቃል ከኛ እንዲወጣ ቃሉ ወደኛ መግባት አለበት። የገባ ይወጣል። ለማንጸባረቅ ደግሞ የተወለወልን መሆን አለብን። ጳውሎስ በ2ቆሮ. 3፥18 *እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመሰል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን* አለ። መስተዋት ከተሸፈነ ወይም አቧራ ከለበሰ የማንጸባረቅ ተግባሩ ይበላሻል። ሁለቱንም ልናደርግ ይጠበቅብናል። በቃልም በኑሮም ምስክር ልንሆን።

ቀጥሎ ጳውሎስ ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ጥቅሶች ውስጥ ስለ ደስታው ይናገራል። በሁለቱ ጥቅሶች ውስጥ 'ደስ' የሚለው ቃል 4 ጊዜ ተጽፎአል። እንደገና ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ እየጻፈ ያለበትን ሁኔታና ቦታ እናስብ። እየጻፈ ያለው ከሮም እስር ቤት ነው። ክርስቲያኖች ከሮም እስር ቤት፥ "ነጻ ናችሁ፤ አምላካችሁን ማምለክ ትችላላችሁ፤ እስራታችሁን ፈጽማችኋልና ውጡና በሰላም ሂዱ" ተብለው አያውቁም። በተለይ ሮማዊ ዜግነት ከሌላቸው ብዙውን ጊዜ በመጫወቻ ሜዳ በተመልካቾች ፊት ለአራዊት እየተሰጡ መጫወቻና መዝናኛ ሆነው ነው የሚሞቱት። ክርስቲያኖች ለቄሳር የማይሰግዱና ሌላ የሚሰግዱለት ጌታ ያላቸው ሰዎች መሆናቸው ለስደትና ለሞት የሚዳርጋቸው ወንጀላቸው ነው። ለብዙዎቹ ድንቅ የሆነው ነገር ግን ሲሞቱ በደስታ መሰዋታቸው ነው።

## ሕያው መስዋዕት እና የሚፈስስ መስዋዕት

ጳውሎስ ከዚህ እስር የሚፈታበትን ጊዜያት የናፈቀባቸው ጊዜያት ቢኖሩም አሁን እዚህ እየጻፈ ያለው ግን የሚሰዋበት ጊዜ እንደቀረበ ተረድቶ ይመስላል። ከሌሎች ሮማዊ ካልሆኑ ክርስቲያኖች ቅጣቱ የሚለየው ምናልባት ለአውሬ ከመሰጠት ወይም በመስቀል ከመሰቀል ይልቅ ቀልጣፋ የሆነ የጨዋ ሞት ቅጣት መቀበሉ ነው። ምናልባት እያሰበ ያለው ተሰይፎ ደሙ የሚፈስስበትን ያንን ቅጣት ነው። በትውፊት የተነገረ የጳውሎስ የሞት ታሪኩ የደሙን መፍሰስ የሚገልጥ ነው። ጳውሎስ በምን ዓይነት አሟሟት እንደሚሞት ቀድሞ የተረዳ ይመስላል። ጳውሎስ ይህንን የሕይወት መፍሰስ በብሉይ ኪዳን ይቀርብ ከነበረው የሚፈስስ መስዋዕት ወይም የመጠጥ ቁርባን (ዘኁ. 15፥1-10፤ 28፥4-7፤ 2ጢሞ. 4፥6) *ጋር ያመሳስለዋል*። በብሉይ ኪዳን ካህኑ መስዋዕት ሲያቀርብ አብሮ የመጠጥ ቁርባን ያፈስሳል። ይህ መስዋዕቱ ከቀረበ በኋላ በላዩ ወይም በአናቱ የሚፈስስ የመጨረሻ ቁርባን ነው። ጳውሎስ እስካሁን የኖረው ኑሮ ራሱ እንደ መስዋዕት ነው፤ ሕያው መስዋዕት። አሁን ደግሞ በመጨረሻና በአናቱ ይህን የሚፈስስ መስዋዕት አድርጎ "ሕይወቴ እንኳ ቢፈስ" ብሎ ሕይወቱን፥ ደሙን የሚያቀርብ ይመስላል። የሥጋ ሕይወቱ በደሙ ውስጥ አይደል ያለው? ዘሌ. 17፥11።

ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ከተለወጠበት ጊዜ ጀምሮ ይህን መልእክት እስከጻፈበት ጊዜ ድረስ ሕያው መስዋዕት ሆኖ ለክርስቶስ በመኖርና በማገልገል ቆይቶአል። አሁን ደግሞ እንደ ብሉይ ኪዳን መስዋዕት በመጨረሻ የሚፈስስ መስዋዕት ወይም ቁርባን ሆኖ ሊያልፍ ተዘጋጅቶአል። ለፊልጵስዩስ ምእመናን የሚነግራቸው ይህንን ነው። እነዚህ በፍቅር ያገለገላቸው ምእመናን ባሳዩት የእምነታቸው መሥዋዕትና አገልግሎት ላይ የእርሱ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ሕይወቱም እንኳ የተሰጠና የፈሰሰ መሆኑ እርሱን ደስ አሰኝቶት እነርሱም አብረውት ደስ እንዲላቸው የጋበዘበት ቃል ነው። ደስታው በሁለቱም፥ ማለትም በፊልጵስዩስ ምእመናንም፥ በጳውሎስም በኩል ነው። በመስዋዕትነት ደስ መሰኘት በእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ የሚከናወን ደስታ ነው።

ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች፥ *ሰውነታችሁን ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ* ብሎ እንደለመናቸው (ሮሜ. 12፥1) ሰውነቱን በአገልግሎቱ ብቻ ሳይሆን ሕይወቱን የሚፈስስ መስዋዕት በማድረግም ሊደመድም የወደደ ሰው ነው። በእርግጥ ሕያው መስዋዕት አድርጎት ኖሮአል። ከልቡ እያገለገለ፥ ያለውን ጨርሶ እየሰጠ፥ በገዛ እጆቹ እየሠራ፥ ሌት ተቀን እየለፋና ለሌሎች እየጸለየ፥ ሳይታክት እያስተማረና እየመከረ፥ ወንጌልን ለማሮጥ ሲል በትዳር ሳይጠመድ ሕያው መስዋዕት ሆኖ ኖሮአል። ያደረገውን ሁሉ በደስታ እያደረገ ኖሮአል። በመከራም እንኳ እየተደሰተ ኖሮአል። ከዓመታት በፊት በፊልጵስዩስ ከተማ ወኅኒ ውስጥ መከራ ሲቀበል ከሲላስ *ጋር* በማኅረምረምና በመመረር ፈንታ በደስታ ዜማ ጌታን እንዳመሰገነው በሮሜም አልተለወጠም። ሞቱን እየጠበቀም ደስ ብሎኛል፤ ደስ ይበላችሁ፤ ደስ ይበለን እያለ ደስታን የሚጽፍ፤ ስሜቱ በሁኔታውና በአካባቢው ያልተለዋወጠ ሰው ነው።

ለኔ ሕይወት ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነው ብሎ በ1፥21 ላይ መስክሮአል። ከዚያ ቀጥሎ ባሉት ጥቅሶችም በሥጋ መኖሩ ለእነርሱ ጥቅም መሆኑን ገልጦ በሚደርስባቸው መከራ እንዳይናወጡ አበረታቶአቸዋል። ሲኖር ለክርስቶስ ስለሚኖር ይህ ደስታው ነው። ከሞተም ወደተሻለው ስፍራ፥ ወደ ጌታውና አምላኩ መገኘት ስለሚሄድ ይህም ደስታው ነው። ለክርስቲያን ከሥጋ ሕይወት ቀጥሎ ወዳለው ሕይወት መተላለፍ ከአንድ ደስታ ወደ ሌላው መሄድ ስለሆነ ለውጥ የለውም። ለውጡ ይኸኛው ሕይወት መከራ ያለበት በመሆኑ ያኛው ይናፈቃል። ጳውሎስ ሞቱ የሰላም ሳይሆን የስቃይና የመሰዋት ሞት ሊሆን እንደሚችል ተረድቶአል።

ክርስቲያን፥ በተለይም አገልጋይ ወደ ሕይወቱ መጨረሻ ሲቀርብ አገልግሎቱን፥ ሕይወቱን፥ ያገለገላቸውን ሰዎች ወደ ኋላ ዞሮ ሲቃኝ ጎዘንና ቅሬታ ሳይሆን ደስታና ሐሴት ልቡን ሲሞሉት እንዴት ውብ በረከት ነው! ይህ የማንም እውነተኛ አገልጋይ የልብ ናፍቆት ነው። ወደ ኋላ ዘወር ብለን ዘመናችንን ስንቃኝ፥ ጥቂትም ከፉም ሆኑብኝ እንዳለው እንደ ያዕቆብ እንዳንሆን ጌታ ይርዳን። የያዕቆብ ዘመኖች ጥቂት ባይሆኑም ክፉ የሆኑበት መቅደም የነበረበትን ባለማስቀደሙ፥ የኋለኛውን ፊተኛ በማድረጉ ይመስለኛል። ጳውሎስ ግን በሕይወቱ ዳርቻ ላይ ሆኖ ዘመኑን ሲቃኝ ቅር የሚለው ነገር አልነበረም። የሚያልፈው እንደ መስዋዕት ሆኖ እንኳ ቢሆን ያንን ሊያደርግ የወደደው በደስታ ነው። ሕይወታችን ሕያው መስዋዕት ሆኖ ሞታችንም ደስታን የተሞላና ያንን የሚያትም እንዲሆንልን ጌታ ጸጋውን ያብዛልን። አሜን።

ዘላለም መንግሥቱ © 2013 (ፀሸሀ፭) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት